# ስለ መጥሪያ አደራረስ እና መጥሪያ ያለ መቀበል ውጤት

በወንጀል ክርክር ጉዳይ ላይ ለተከሳሽም ሆነ ለምስክሮች መጥሪያ የሚያደርሰው ፖሊስ ሲሆን አንድ ሰው /ተከሳሽም ሆነ ምስክር/ የፍርድ ቤት መጥሪያ ደርሶት እና ፈርሞ በቀጠሮ ቀን ያለ በቂ ምክንያት ሳይቀርብ ከቀረ ታስሮ እንዲቀርብ የሚታዘዝ ይሆናል፡፡ ፖሊስ ተከሳሹን በአካል አግኝቶ ለመስጠት የማይቻል እንደሆነ እና ተከሳሹ የተከሰሰበት ወንጀል ከ12 አመት በላይ የሚያስቀጣ ወይም በወንጀል ሕግ አንቀጽ 343 እስከ 354 ድረስ የተዘረዘሩት በመንግስት የኢኮኖሚ እና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሆነው በጽኑ እስራት ወይ ከ5000 ብር በላይ ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል የተከሰሰ ከሆነ ፍርድ ቤቱ መጥሪያ በጋዜጣ ወይም ሌላ አመቺ ነው ብሎ ባመነበት በሌላ መንገድ እንዲደርስ ይታዘዝና ነገሩ ተከሳሽ በሌለበት ይሰማል፡፡

በፍትሐ ብሔር ጉዳይ መጥሪያ ለተከሳሽ የሚያደርሰው ከሳሽ እራሱ ሲሆን መጥሪያውን የሚቻል በሆነበት ጊዜ ሁሉ ለተከሳሹ ለእራሱ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ነገር ግን ተከሳሹን ማግኘት ካልተቻለ መጥሪያ መቀበል ለሚችል የሚያስችል ውክልና ላለው ወኪሉ፣ ወኪል ከሌለው 18 አመት በላይ የሆኑት አብረውት ለሚኖሩ የቤተሰብ አባላት፣ ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ ካለው ለጠበቃው ወይም ነገረ ፈጁ በእጁ በመስጠት ወይም ቢሮው በማስቀመጥ መጥሪያ መስጠት ይቻላል፡፡ ተከሳሹ የመንግስት መስሪያ ቤት ከሆነ ለነገረ ፈጁ ወይም ለመዝገብ ቤት መጥሪያ መስጠት ይቻላል፡፡ ተከሳሹ ወኪል የሌለው ከሆነ እና የጦር ሰራዊት አባል ሲሆን መጥሪያው ለክፍሉ አዛዥ የሚሰጥ ሲሆን ተከሳሹ እስረኛ ከሆነ ለታሰረበት ማረሚያ ቤት ሀላፊ መጥሪያ ተልኮ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

የተከሰሰው የንግድ ድርጅት ከሆነ መጥሪያውን ለዋና ፀሀፊ፣ ከኩባኒያው ዳይሬክተሮች ለአንዱ በመስጠት፣ ድርጅቱ የታወቀ የተመዘገበ አድራሻ ካለው መጥሪያውን በአካል በመውሰድ ወይም በፖስታ በመላክ ማድረስ ይቻላል፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ የታወቀ አድራሻ ከሌለው የንግድ ሥራውን በሚያከናውንበት ስፍራ በፖስታ በመላክ መጥሪያውን ማድረስ ይቻላል፡፡ ተከሳሹ የሚኖረው መጥሪያውን ካዘዘው ፍርድ ቤት ግዛት ክልል ውጪ የሚኖር ሆኖ ተከሳሹ የንግድ ሥራ በፍርድ ቤቱ ግዛት ውስጥ የሚሰራ ከሆነ መጥሪያው በታዘዘበት ወቅት በፍርድ ቤቱ ግዛት ክልል ውስጥ ለሚገኘው ወኪሉ ወይም ሥራ አስኪያጁ የተሰጠ ከሆነ ለእራሱ እንደተሰጠው ይቆጠራል፡፡ በመሆኑም በዚህ መሠረት በአንድ መርከብ ላይ አዛዥ የሆነ ግለሰብ የመርከቡ ባለቤት ወይም ተከራይ ወኪል እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

የሽርክና ድርጅት በድርጅቱ ስም ተከስሶ የሚሰጥ መጥሪያ ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከሽሪኮቹ ላንዱ ወይም ከአንድ ለበለጡት፣ ድርጅቱ ዋነኛ ሥራውን በሚከናውነው አድራሻው በኩል ድርጅቱን በበላይ ተቆጣጣሪነት ለሚመራው ሰው በመስጠት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ መጥሪያው በኢትዮጵያ ላሉትም ለሌሉትም ሽሪኮች እንደደረሰ ይቆጠራል፡፡ መጥሪያው ለአንድ ድርጅት አባል ብቻ የሚላክ ከሆነ ለተላከለት ሰው መጥሪያው የተላከው በሽሪክነቱ፣ በአባልነቱ ወይም በበላይ ተቆጣጣሪነቱ መሆኑ በጽሁፍ ሊገለጽለት የሚገባ ሲሆን ይህ ካተገለጸ ግን መጥሪያው የተላከለት በሽርክናው ብቻ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

ክሱ የቀረበው በማይንቀሳቀስ ንብረት /ቤትና ይዞታ/ ላይ ወይም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በደረሰ ጉዳት ካሳ ለመጠየቅ ከሆነ መጥሪያውን በዚህ ንብረት ላይ ለሚገኝ ጠባቂ ወይም በንብረቱ ላይ ለሚኖር ሰው መስጠት በቂ ሲሆን በዚህ መልኩ የደረሰ መጥሪያ ለባለቤቱ ለእራሱ እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት መጥሪያ ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎች መጥሪያውን ፈርመው መቀበል ያለባቸው ሲሆን መጥሪያ ለመቀበል ወይም መተማመኛ ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆኑ ይህ በቃለ መሐላ ወይም በሌላ መንገድ የተረጋገጠ እንደሆነ መጥሪያው እንደደረሳቸው ተደርጎ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የሚታዘዝ ይሆናል፡፡ ይህ የሚሆነው የክስ መጥሪያ ለተከሳሽ በሚላክበት ወቅት ሲሆን መጥሪያው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መጥሪያ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሽ /የፍርድ ባለ ዕዳው/ ታስሮ እንዲቀርብ ሊያዝዝ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ምስክር መጥሪያ ደርሶት ያለ በቂ ምክንያት በቀጠሮ ቀን ሳይቀርብ ከቀረ ታስሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

መጥሪያ እንዲያደርስ የታዘዘ ከሳሽ መጥሪያ አስፈርሞ ሲያደርስ መጥሪያ ያደረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ይህ ማረጋገጫ መጥሪያ የደረሰበትን ጊዜ፤ የተቀባዩን ስም ሲቀበል የነበሩትን ሰዎች ስም ከሚገልጽ ጽሁፍ ጋር ተቀባዩ የፈረመበትን መተማመኛ ዋና ግልባጭ አያይዞ ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

ተከሳሹ መጥሪያ እንዳይደርሰው የተሸሸገ ወይም እንዳይደርሰው መሰናክል ያደረገ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ያወቀ ከሆነ መጥሪያውን በፍርድ ቤቱ ጊቢ ውስጥ፤ በተከሳሹ መኖሪያ ቤት ፤ የመጨረሻ ይኖርበት የነበረበት አድራሻ፤ ወይም የንግድ ሥራውን በሚሰራበት አድራሻ ላይ እንዲለጠፍ በማድረግ ወይም በጋዜጣ እንዲወጣ የሚደረግ ሲሆን ይህ መጥሪያ ለተከሳሹ ለእራሱ እንደተሰጠው ይቆጠራል፡፡

ተከሳሹ ውጭ ሀገር የሚኖር ሲሆን እና አድራሻው የታወቀ ከሆነ እና መጥሪያ የሚቀበል ወኪል የሌለው ከሆነ መጥሪያ ለሚኖርበት ሀገር በፖስታ እንዲላክ የሚደረግ ሲሆን አድራሻው የማይታወቅ ከሆነ ግን መጥሪያው በጋዜጣ እንዲወጣ የሚደረግ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ተከሳሹ ከሀገር ውጪ የሚኖር ባይሆንም ፍርድ ቤቱ መጥሪያ ለተከሳሽ ወይም ለወኪሉ በአድራሻው በአደራ ፖስታ እንዲላክ ሊያዝዝ ይችላል፡፡

ተከሳሹ የሚኖረው በሀገር ውስጥ ሆኖ ነገር ግን ከፍርድ ቤቱ ግዛት ክልል ውጪ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሚኖርበት አከባቢ ለሚስችለው ፍርድ ቤት መጥሪያውን በመላክ ለተከሳሽ እንዲደርሰው ሊያዝዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም ተከሳሹ የሚሰራው በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የግል ድርጅት ውስጥ ከሆነ እና ለመጥሪያ አሰጣጡ ምቹ ነው ተብሎ ካሰበ ፍርድ ቤቱ መጥሪያ ለተከሳሹ በሚሰራበት መስሪያ ቤት በኩል እንዲደርሰው መጥሪያውን ለድርጅቱ ሀላፊ ሊልክ ይችላል፡፡